Calgary

# Livery Transport Services

**መፅሔት #007**

**LTS (ላይቨሪ የትራንስፖርት አገልግሎቶች) የፈቃድ መስጫ ክፍያ ማሻሻያ** **2021 መጋቢት 29**

ባለፈው ዓመት በሙሉ፣ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በታክሲ እና በሊሙዚን ኢንዱስትሪ ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩን ቀጥሏል። ለኢንዱስትሪ ተሳታፊዎች የፋይናንስ ችግርን በመገንዘብ፣ አስተዳደሩ መጋቢት 15፣ 2021 ለከተማ ምክር ቤት ሪፖርት በማቅረብ እስከ ግንቦት 14፣ 2022 ድረስ የፍቃድ እድሳት ክፍያዎች ቅነሳ እንዲደረግ ጠይቋል።

የከተማው ምክር ቤት የሚከተሉትን አጽድቋል፦

- የታክሲ እና የሊሙዚን መንጃ ፈቃድ እድሳት ክፍያዎችን እንስቷል ($141 → $0)
- የታክሲ ታርጋ ፈቃድ እድሳት ክፍያን በ50 በመቶ ቀንሷል ($912 → $456)
- የሊሙዚን ታርጋ ፈቃድ ዕድሳት ክፍያን በ50 በመቶ ቀንሷል ($731 → $365.50)

ለማስታወስ ያህል፣ አሽከርካሪዎች አሁንም የታክሲ እና/ወይም የሊሙዚን መንጃ ፈቃዳቸውን እንዲያድሱ ይጠበቅባቸዋል፤ ይህም የካልጋሪ የፖሊስ አገልግሎት መረጃ ማረጋገጫን ማጠናቀቅን ያካትታል። እባክዎን ያስተውሉ፣ የታክሲ ታርጋዎች በሰኔ እናም የሊሙዚን ታርጋዎች በመስከረም ይታደሳሉ።

ማንኛውም ጥያቄዎች ካለዎት፣ እባክዎን ለቢሮአችን በ LTSengagement@calgary.ca ኢሜይል ይላኩ።

ከሰላምታ ጋር፣



አብዱል ራፊህ
ዋና የላይቨሪ ተቆጣጣሪ
የካልጋሪ ማህበረሰብ ደረጃዎች